# የፖለቲካ ቁማርተኞቹ የጥፋት እጆቻቸውን ይሰብስቡ

አዲሱ ለማ

ኢትዮጵያ የተፃፉ ህገ መንግሥት ካሏቸው የዓለማችን አገሮች አንዷ ናት፡፡ ህገ መንግሥቱ የዜጎችን የማሠራት፣ ከቦታ ቦታ የማዘዋወር፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦችና የፆታ እኩልነትን፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ የኃይማኖት ነፃነትን፣ በቋንቋ የመጠቀምንና የመሟርን በአጠቃላይ ተዘርዝረው የሚያልቁ መብቶችን የሚያከብርና የሚያስከብሩ አንቀጾችን ይዟል፡፡

በዚህም ከየትኛውም አገር በተለየ ሜሌኩ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት፣ ነፃነትና መብት እስከ ማንጠል የሚሌ በይዘቱም ይሁን በዓይነቱ ዘመናዊና በዓለም ሊጠቀስ የሚቻል ደረጃ ያለው ህገ መንግሥት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ከላይ የተዘረዘሩቱን መብቶች ሁሉ ቢሰጥም መብቱን አወቆና ህግ አክብሮ በነፃነቱ ማጠቀም የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡

ኢትዮጵያወያን ከመቼወም ጊዜ በበለጠ በዜግነታቸው የሚገባቸዋን ደሞክራሲያዊ መብትና ነፃነት ማግኘታቸዋን በተግባር አረጋግጠዋል፡፡ ከእነዚህም ህገ መንግሥታዊ መብቶች ሚረጋገጫዎች በየአምስት ዓመቱ የሚከሄደው አገር አቀፍ ምርጫ በማሣያነት ይገኝበታል፡፡ ዜጎች የፈለጉትን የመናገር፣ የማምረጥ ሙሉ ነፃነታቸዋን ተጠቅመው የሚያደርጉት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ ከህገ መንግሥቱ በሚምነጭ መብት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሠላምና በአንድነት በመከባበርና በመተባበር ማንም የፈለገወን ኃይማኖት ቢከተል መንግሥትም በኃይማኖት፤ ኃይማኖትም በመንግሥት ጣልቃ አይገቡም፡፡ እናም ይህ የህገ መንግሥቱ አንቀጽ የዜጎችን ነፃነት፣ ባለቤትና ተጠቃሚ መሆኑን ለማስረዳት ያለመና ያጎናፀፈም ነው፡፡

የአፌዴሪ ህገ መንግሥት ይህንን ያህል የተብራራና የተተረጎመ ሆኖ ሳለ ዛሬ…ዛሬ አንዳንድ ዜጎች ኃይማኖትን ሽፋን አድርገው ሕዝብን ከሕዝብ፤ ሕዝብን ከመንግሥት ለሚጋጩ ሴራ ጠንስሰው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ሁኔታወን ደርሰወበታል፡፡

የእነዚህ ወገኖች ቅሬታ ሲፈተሽ ሜላወን የእሥልምና ኃይማኖትና ተከታዮቹን የሚይወክል ሆኖ ይታያል፡፡ ቅሬታቸወን በህግና በህግ አግባብ ብቻ ለማስገንዘብና ለመፍታት ከመንቀሳቀስ ይልቅ በአመፅና ኃይማኖቱን ሽፋን በሚድረግ ተበዳይ ማስሎ ለመታየት ይሞክራሉ፡፡

ሕዝበ ሙስሊሙ በአገሩ በሠላምና በነፃነት ህግን አክብሮ ህገ መንግሥቱ ያጎናፀፈወን መብቱን እየተገበረ ኃይማኖቱን የማካሄድ ሙሉ ድጋፍ አለው፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ጥቂት ወገኖች የኃይማኖቱ አባቶችና ሚዎች ከሚያውቁት ውጭ ኃይማኖታዊ ቅሬታ ሳይሆን ፖለቲካዊ ችግር ለማስመሰልና አገር አቀፋዊነት ለማስያዝ ይፍጨረጨራሉ፡፡

መንግሥት ሁኔታወን በቅርበትና በትዕግሥት እየተከታተለው ይገኛል፡፡ ጥቅምት 27 ቀን 2005 ዓ.ም በመላ አገሪቱ በሠላም፣ በዴሞክራሲያዊና በነፃነት የተካሄደው የኡለማ ዳዕዋዎች ምርጫ በስኬት ማጠናቀቁ ሲታይ የእነዚያ ወገኖች እቅድ ምን እንደነበር ለማወቅ አያስቸግርም፡፡

የሕዝበ ሙስሊሙ በነቂስ ወጥቶ ለመምረጥ ያደረገው ሂደትና ወጤቱ ምርጫው ፍትሃዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ነፃ እንደነበር ሂደቱን የተከታተሉ የእምነቱ ተከታዮችና የኃይማኖት አባቶች እንዲሁም መራጩ ራሱ ሕዝበ ሙስሊሙ በሰጠው አስተያየት ገልጿታል፡፡

የእነዚያ ጥቂት በኃይማኖቱ ሽፋን ተከልለው የሁከትና ብጥብጥ አጀንዳ የነበራቸው ወገኖች ሴራ ከሸፈ፤ በኢትዮጵያ የኃይማኖቶች መቻቻልና እኩልነት፤ ኃይማኖቶች በጋራ በሠላምና በመተሳሰብ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ልማትን፣ እድገትንና ሠላምን የሚያብቡበት አካሄድ ማስፈኑን ድጋሚ ታየ፡፡

ሕዝበ ሙስሊሙና ሌሎች የኃይማኖት ተከታዮችን እንዲሁም መንግሥትን ለማጥቆር ከርቀት የከሰረ ፖለቲካ ሾተላቸውን ይዘው የጥላቻ፣ የቁርሾ፣ ያለመተማመንና ያለሚጋጋት እሣት በአገሪቱ ወስጥ እንዲነድ የሚቆሰቁሱ፤ ግለኝነት የተጠናወታቸው፤ የአገር መልካም ገፅታ የሚያታያቸው፤ ሁሌም የጎዳና ላይ ነውጥን የሚሹ፤ የወገን ችግርና ሰቆቃ የሚያስማቸው፤ የግል ሀሳባቸውንና ፍላጎታቸውን በኃይል ለመጫንና ለማራገፍ የሚታትሩ የከንቱ ምኞት ሰለባዎች ናቸው፡፡

በተለይም ኃይማኖትን ሽፋን በማድረግ የአገርን ገፅታ ጥላሸት ለመቀባትና በአገሪቱ ወስጥ ምንም ዓይነት የኃይማኖት ነፃነት እንደሌለ በማስመሰል ሕዝበ ሙስሊሙን አንድ ጊዜ ከሌሎች ኃይማኖቶች፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከመንግሥት ጋር፣ ሲያሻቸውም ከራሱ ከሙስሊሙ ጋር እርስ በርስ ለማጋጨት የተለያዩ ሴራዎች ሲሸረቡ ኖረዋል፡፡

በዚህ ሳያበቃም የብጥብጡን ጭፍ ከዳር ለማድረስ የአክራሪነት ስሜት የተላበሱ ጥቂቶች ያስነሱትን ተቀጣጣይ የመሰላቸውን የአመፅ እሣት ሕዝበ ሙስሊሙ ያለማንም ቀስቃሽ በንቃትና የጀመሩትን አሣፋሪ ተግባር በንቀት አከሸፎ አጋልጧቸዋል፡፡

ያ አስፀያፊና አሣፋሪ የአገርን ገፅታና የአገርን ታሪክ የሚያጎድፍ ተግባር ሕዝቡ ሊያስተናግደውና ለሸከመው ቀርቶ ለሰማውና ሊያስበው አይፈልግም፡፡ የዚያ ዓይነት የአክራሪና አሸባሪነት ጽንሰ ሀሳብ

አራማጅነት አቋም የያዙትን ወገኖች በድብቅ ካሉ እንኳ ኢትዮጵያ የእነርሱን አቋም ሚራመጃ የማያን የተመቻቸና ፍፁምም የሀሳቡን ማስጠለያ ሥፍራ እንደሌላት በተደጋጋሚ አስገንዝቧል፡፡

ከዚህም ዓይነት ፍሬ አልባ ተግባር ወደ ሠላማዊና ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲመለሱ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ እየተሰሩም ነው፡፡

በዓለማችን ላይ በተለይ በአንዳንድ አገራት በታየው የአክራሪነት አሻራ ያረፈባቸው አገሮች በሕዝቦች መካከል ጥላቻ ቁርሾና ያለመተማመን አደጋዎች ሲጋረጥ ታይቷል፡፡

በቅርብ በምናውቃት ሶማሊያ የችግሩ ወጠቂ ከሕፃናት እስከ አቅመ ደካማ አዛውንቶች፤ ከአርብቶ አደሩና ሰርቶ ከሚያድረው እስከ ምሁራኑ፤ እንዲሁም የጦር ኃይሉ ሳይቀር ነፍጥ አንስቶ እርስ በርስ እንዲፋጅ በእሣት ላይ ቤንዚን ያርከፈከፉበት ወቅትን እናስታውሳለን፡፡

የአክራሪነትን ስሜት ይዘው የተነሱት እነዚህ ጋጠ ወጦች የዓለም ሕዝብ መነጋገሪያ አጀንዳ ከሆኑ ከራርመዋል፡፡ ይህንኑ እኩይ ተግባራቸውን የዓለም ሕዝብ ማውገዝ ከጀመረም ሰነባብቷል፡፡

አገራት በጋራ ጽንፈኞችንና አክራሪዎችን በእንጭጩ ሲሆን ከከፉ መንገዳቸውና ሀሳባቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ብርቱ ጥረቶችን ፈጽመዋል፡፡ ሕዝቦቻቸውን በማስተማር ግንዛቤ በማስረፅ የዚያ የአክራሪነት ሰለባዎች እንዳይሆኑ ሲከላከሉ ይስተዋላሉ፡፡

በሌላ በኩል የአክራሪነትን ስሜት ሕዝቦቻቸው ማሸከም እንደሚችሉ የተገነዘቡና ብዙ የሰሩ አገሮች የዚያን ዓይነት ጽንሰ ሀሳብ አራማጆችን ገና ከጅምሩ የሚያመክኑበት አሠራር ዘርግተዋል፡፡

ኢትዮጵያም ሕዝቦቿን ከዚያ ዓይነት የአክራሪነት ጽንሰ ሀሳብ ሚናብ ለመካላከልና ለማጠበቅ ብቻም ሳይሆን ሀሳቡ ፈፅሞ ወደ ተግባር እንዳይለወጥ ጠንክራ በንቃት እየሰራች ለመሆኑ ዛሬ ላይ ሌላ ምስክር አያስፈልግም፡፡ የሠላሙ የልማቱና የዴሞክራሲ ተጠቃሚ የሆነው ሕዝበ ሙስሊሙ ቀዳሚ ተሰላፊ ነውና፡፡

እነዚህ የአክራሪነት ጽንሰ ሀሳብ የያዙና የተንቀሳቀሱ ጥቂት ወገኖች ዓላማቸው እንዲሁም ግባቸው ምን እንደሆነ ራሳቸው አልተገነዘቡትም አሊያም አያወቁትም፡፡

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የኃይማኖት ሆነ የፖለቲካ ችግር አለ የሚል ወገን ካለ ሀሳቡን አቅርቦ በሠላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀስበት መንገድ ተመቻችቷል፡፡ ነገር ግን በአገራችን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በጥቂቶች እየታየ የነበረው መንፈስ ሌሎችን ከማባከሉ በፊት ሕዝበ ሙሥሊሙ ከመንግሥት ጋር በመቀናጀት በሰፊው በከወነው ተግባር ጽንፈኞቹ የተንጠለጠሉበት ትልቁ ማሳላቸው ተሰብሯል፡፡ እንዲሁም አከርካሪያቸው ተመትቷል፡፡

እናም በኢትዮጵያ ምድር የዚህ የአክራሪነት ጽንሰ ሀሳብ ከአራማጆቹ ብቻም ሳይሆን ከአማኞቹ አዕምሮ እንዲጠፉ ተደርጓል፡፡ ሕዝበ ሙስሊሙ ህገ መንግሥቱ ባጎነፀፈው የዴሞክራሲያዊ መብቱና ነፃነቱ ተጠቅሞ ኃይማኖቱን ይመሩልኛል ብሎ ያመነባቸውን ኡለማዎቹን መርጧል፡፡

እነዚያ ከውጭ ሆኑው በረዥም ዘንግ አገር ቤት የሚያነዱትን እሣት ለመቆስቆስ የሚጥሩትን የአሸባሪነት ጽንሰ ሀሳበ መፍለቂያ ቡድኖች ሕዝበ ሙስሊሙ በኢትዮጵያ ይህኛውም በር አያስገባችሁም ብሎ ዘግቶባቸዋል፡፡

በውጭ ሆነው የአመጽና የጎዳና ላይ ነውጥ በአገራቸው ላይ እንዲከፈት የሚያስቡ ቡድኖች ቡድናዊ ስሜታቸውን ሕዝቡ ሊሸከምላቸው አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲሁም ሕዝበ ሙስሊሙ በአንድ ሀሳብ ሴራቸውን ከወዲሁ አወቆ እየተከታተላቸው ነው፡፡

ሕዝቡ በኢትዮጵያ ምድር ከእንግዲህ ልማትና እድገት እንጂ ብጥብጥ ሞትን አንፈልግም ብሎ በከፍተኛ ቁርጠኝነት ተነሳስቷል፡፡ ከውጭ ሆነው እንደ እነ ግንቦት 7 መሰል አሸባሪ ድርጅቶች በሚዘሩት ወሻንብር ተገፋፍቶ የሚገባበት የጎዳና ላይ ነውጥ እንደሌለም ሕዝቡ በተደጋጋሚ አረጋግጧል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በተለይ ሕዝበ ሙስሊሙ በቅርቡ ባደረገው ነፃ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ የኃይማኖቱ መሪዎች ምርጫ ላይ አሳይቷቸዋል፡፡ እነዚህ ከውጭ ሆነው አገር ውስጥ የአፍራሽ ፖለቲካ እሣት ለማንደድና ለመቆስቆስ በከንቱ የሚደክሙ ወገኖች ሴራ የሚራገበው እንደ እነ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ /ቪ.ኦ.ኤ/ ባሉ መገናኛ ብዙኃን አማካይነት ነው፡፡

ከዚህም ጋር በአሸባሪነት ጽንሰ ሀሳብ ስሜት በተሞሉ፤ ፍፁም የአገርና የሕዝብ ሠላም በማይታያቸው፤ ኃላፊነት በጎደላቸው፤ የጋዜጠኝነት ሥነ ምግባር በሌላቸው ጥቂቶችና ለዚሁ የብጥብጥ ተግባር ተብሎ በተሰየመው የኢሣት ልሣን በተወከሉ፤ ለግል ጥቅም በሚሰሩ ሰዎች እንዲሁም በአገር ውስጥ ተቀባይነት ባጣው ፖለቲካው ትዝብትን ባተረፈው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ከንቱ መፍጨርጨር ነው፡፡

የመላው ዓለም ትኩረት ወደሆነው የሽብርና ሽብርተኞችን የአክራሪዎችንና አክራሪነትን ሴራና ምንጭ የማድረቅ ትግል በተገባበት በዚህ ዘመን የዚህም ትግል ፊታውራሪ ናት ተብሎ ከሚነገርላት አሜሪካ የዓለም ሕዝብ ከፍተኛ ድርሻ ይጠበቃል፡፡

ነገር ግን ከአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ጋር የሚጣረስ ተግባር የሚፈፅመው የአሜሪካን ድምፅ ራዲዮ እንዲሁም ኢሣት ከግንቦት 7 ጋር ሆኖ የሚያራግቡት የሽብር ተግባር መቀመጫቸውን አሜሪካን ያድርጉ እንጅ የሽብርተኝነትነም ሆነ የአክራሪነትን ተግባር ለማስፈፀም የሚጥሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡

የዚህ ዓይነቱ እሣትን በጉያ የመደበቅ ዓይነት ጨዋታ አንድ ቀን እሣቱ በጉያው የያዘውን ሰው ማቃጠሉ አይቀርም፡፡ ይህንን ደግሞ ከራሷ ከአሜሪካን በላይ ተሞክሮውን የሚያውቀው የለም፡፡ ሽብርተኝነትን እየተዋጉ ሽብርተኛ ቡድንን ማስጠለል ምን ማለት ይሆን?

በኢትዮጵያ ያለው ሠላም፣ ደሞክራሲና ልማት ዓለምን ያስደመመ ሀቅ ሆኖ ሳለ የእነዚህ ብጥብጥ ናፋቂ ሴረኞች ደባ ለምን አስፈለገ? የአገር ልማትና እድገት ለሕዝቦቿ ነው፡፡ ሌላ ለማንም አይደለም፡፡

ኢትዮጵያ የጦርነትንና የሰቆቃን፣ የረሀብንና የችግር እንዲሁም የክፉ ቀንን ትርጉም በሚገባ ታውቃቸዋለች፡፡ አሁን እያጣጣመች ያለው የሠላምን የደሞክራሲን፣ የልማትንና የዕድገትን ፍሬዎች ነው፡፡ ወደ ትናንቱ የክፉ ቀን ጨለማ ካልተመለሰች ብሎ ሴራ መሸረብ ከግለኝነትና ጨለምተኛ አስተሳሰብ የሚመነጭ አረመኔያዊነት ነው፡፡

የግል ጥላቻና ቂምን በቡድን ለመግለጽ መሞከር፣ የግል ጥላቻንና ቂምን በኃይማኖት ሽፋን ለመግለጽ መንቀሳቀስ አሳፋሪና አስነዋሪ፤ ከትዝብት ባለፈ ሕዝባዊ ቅጣትን የሚያስቀጣ ተግባር ነው፡፡

አገሪቱ በአሁኑ ጊዜ ይልቁንም ከአፍሪካም ይሁን ከዓለም አገራት ጋር በሠላምና በደሞክራሲ መርህ ተቀባይነቷና ተሰሚነቷ እየጨመረ መምጣቱ የማንና የምን ውጤት መሆኑን የሚያስተውሉ ፈፅሞ የሚዘነጉት ጥቂቶች የሚዘሩት የአሉባልታ ወይም የተረት ተረት ፈሊጣቸው ከኖሩበትና ካሉበት የእድሜ ቁጥር አንፃር በእጅጉ ሊያሳፍራቸው በተገባ ነበር፡፡

ነገር ግን ካፈርኩ አይመልሰኝ ዓይነት ሆነና በጥፋታቸው ላይ ሌላ የጥፋት ዓይነት ለመጨመር አቅጣጫቸውን ቀይረው በኃይማኖት ተቻችሎና ተከባብሮ፣ ተፋቅሮና ተፈቃቅዶ፣ ለዘመናት የኖረውን ሕዝበ ሙስሊሙን ከወገኑና ከመንግሥት ጋር ለማጋጨት ብሎም በአገሪቱ ሠላም እንደሌለ ለማስመሰል የተጠነሰሰው ሴራ ባለፈው መስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም በአገሪቱ በሕዝብ ሙስሊሙ ወገን በተካሄደው ምርጫ በግልጽ ታይቷል፡፡

በዚህ በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በተካሄደው የዳዕዋዎችና ኡላማዎች ምርጫ በኃይማኖቱ ሽፋን ያሰቡትን ለማስፈፀም ወጥኑ የነበራቸው ጥቂቶች ምርጫው በማስጊድ ካልሆነ ብለው ሀሳባቸውን ማንፀባረቃቸውም ይታወሣል፡፡

ይህ ከሆነ ደግሞ ያሰቡትን ለሚፈፀም ሲንቀሳቀሱ የፀጥታ አስከባሪዎች ከአስነዋሪ ድርጊታቸው ሊቆጣጠሯቸው አይችሉም እናም የሠላማዊ ሕዝበ ሙስሊሙን የምርጫ ሂደት ላይ ጋሬጣቸውን በማጋረጥ የአገርን ገፅታ ለማበላሸት አመቺ ይሆንላቸዋል፡፡

ነገር ግን እነዚህ ጥቂት የጥፋት ኃይሎች ያቀዱትን እንዳይፈፅሙ ሕዝበ ሙስሊሙ ቅዱስ ሥፍራዎቹንም ከሚያረክስ ድርጊት ማጠበቅ ስላለበት እቅዳቸው ከከንቱ ህልም ያላለፈ ቅዠት ሆኖ መክኖባቸዋል፡፡

ሠላማዊውና ህገ መንግሥቱ ያጎናፀፈውን የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ለመተግበር የሚያመቻቸውን ቦታ በወል ያወቀዋልና ባለበት የቀበሌና አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች ሁሉ በነፃነትና በዴሞክራሲያዊ መብቶቹ በመጠቀም የሚጣቸውን ሚጦ ኃላፊነቱንና አደራውን ሰጥቷቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ይህ ከመስጊድ ውጭ የተደረገው ምርጫ ለሙሥሊም እህቶቻችን ፍፁም የተመቸና የእነርሱን ህገ መንግሥታዊ መብትም ከግምት ወስጥ ያስገባና ሰፊ ዕድል የፈጠረ በመሆኑ ይህ ምርጫ በአገራችን የእሥልምና ኃይማኖት ታሪክ ፍፁም ያልታየና ታሪክ በልዩ ሥፍራ የሚያስቀምጠው ሀቅ ነው፡፡

ይህም በእያንዳንዱ ሕዝበ ሙሥሊም የልብ የክብር ማዘገብ ወስጥ በክብር የተቀማጠ ነው፡፡ እንዲሁም ለመላው የአገራችን ሠላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ፈላጊ ሕዝቦች የአገሪቱ መንግሥት ለሁሉ ኃይማኖቶች እኩልና ተመሣሣይ መብት ያጎናፀፈውን ህገ መንግሥት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያገብረው፣ እንደሚጠብቀው፣ እንደሚያከብረውና እንደሚያስከብረው በግልጽ የታየበት የታሪክ ክስተት ነው፡፡

በዚህ አጋጣሚ ሕዝቦች በሚፈቃቀድ መከረውና ፈቅደው ያፀደቁትን ህገ መንግሥትና ሥርዓት የማጠበቅና የመንከባከብ፣ የማክበርና የማስከበር በዚያም የመጠቀም መብትንና

ነፃነትን የተጎናፀፈው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ኃላፊነቱ መሆኑ ሊሰመርበትና አፅንኦት ሊሰጠው ይገባል፡፡

መንግሥት የአገርንና የሕዝቦች ሠላምና ፀጥታ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የማጠበቅ ሕዝባዊና ታሪካዊ አደራና ኃላፊነት አለበት ግዴታውም ነው፡፡

በዚህ ኃይማኖትን ሽፋን አድርጎ የመንቀሳቀስ የከሰረ ፖለቲካ ግብ የለሽ ዓላማ ለማሳተፍ የሚደረግን ማንኛውም ጥረት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ከምንጊዜውም በበለጠና በልዩ ትኩረት እየተከታተሉ ጥፋተኞችን ለህግ በማቅረብ የእጃቸውን እንዲያገኙ ማድረጉን ይቀጥላል፡፡

ከዚያ በፊት ግን የዚህ ዓይነት አክሳሪ የፖለቲካ ቁማርተኞች ያሰሉትን ስሌት የሚከተሉ በአገርም ወስጥም ይሁን በውጭ የሚኖሩ ጠስ የሚዘሙቁ ግለሰቦች ወደ ሕሊናቸው ተመልሰው ደጋግመው እንዲያስቡና በሚያደርሱት ጥፋት ተጎጂው አገርና ሕዝብ መሆኑን እንዲሁም ለሚያደርሱት ጥፋት ፍርዱንና ቅጣቱን የሚሰጣቸው የኢትዮጵያ ሠላምና ልማት ወዳድ ሕዝብ መሆኑን ተገንዝበው እጃቸውን እንዲያሳርፉ ጥሪው ይድረሳቸው፡፡